

ግብረ-ገብ ትምህርት

የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ

1ኛ ክፍል

አዘጋጆች፡-

- **ትዕዛዙተምትሜ** (M.A)
- **ዘውዱ ተምትሜ** (M.A)

አስማምዶ አዘጋጆች፡-

- **አሸናፊ ፍሰሐ** (M.A)
- **አዳነ ይርጉ** (M.A

አርታኢዎች፡-

- **አለማየሁ ነጋሽ** (PhD)
- **ቃለወንጌልምናለ** (PhD)
- **ሙሉጌታ ያየህ** (PhD)

ሰዓሊዎች

- **ኤልዛልሞን ጌቱ**

የሽፋን ሥዕል

- **ናትናኤ ጢብእሸት**

የይዘት አርታኢ

- **ሳባ መንግስቱ**

የይዘት አርታኢ

- **ወዳጀነሽ አሸንጎ**

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው ተሸፍኖ ሲሆን፤ በኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እንዲሁም በአርባምንጭ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በ አማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቷል፡፡ የመጽሐፍ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

ለመጽሐፉ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ከመሆኑም በተጨማሪ በቀጣይ ታናናሾቻችሁ የሚማሩበት ስለሆነ መጽሐፉ እንደይቀደድ ወይም እንዳይበላሽ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለጥንቃቄ የሚረዱ የሚከተሉትን 11 ነጥቦችን ልብ በሉ።

1. የመጽሃፉን ደህንነት ለመጠበቅ በፕላስቲክ፣ በአሮጌ ጋዜጦች ወይም መጽሔቶች ሸፍናችሁ ያዙ።
2. መፅሃፉን ሁልጊዜ ንጹህና ደረቅ በሆነ ቦታ አስቀምጡት።
3. መጽሐፉን ስትጠቀሙ እጆቻችሁ ንጹህ መሆናቸውን አረጋግጡ።
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይም ይሁን በዉስጥ ገጾቹ ላይ ምንም ዓይነት ጽሁፍ አትጻፉ።
5. መጽሀፉን ሲይዙ እንዳይበላሽ ወረቀት ወይም ካርቶን ይጠቀሙ።
6. በመጽሀፉ ውስጥ ያለ ማንኛውንም ስዕሎች ወይም ገጾች ፊጽሞ አትቅደዱ ወይም አትቁረጡ።
7. በመጽሀፉ ውስጥ የተቀደዱ ገጾች ካለ በመለጠፍ ወይም በመጠገን ተጠቀሙ።

8. መጽሐፉን በትምህርት ቤት ቦርሳ ውስጥ ስታስገቡም ሆነ ስታወጡ በጥንቃቄ አድርጉት።
9. መጽሐፉን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ስትጠቀሙ በጥንቃቄ ተጠቀሙ።
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ በጀርባው አስቀምጡት።.
11. በአንድ ጊዜ ጥቂት ገጾችን ብቻ ክፈቱ፤እንዲሁም ገጾቹን በምትቀይሩበት ጊዜ ከታሰረው ጠርዝ ጋር ትንሽ ተጫኑ። ይህም ሽፋኑን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ያደርገዋል።.

ማውጫ

መግቢያ vii

ምዕራፍ አንድ 1

የልጆችራሰን መቆጣጠር /ሰነ ሰርአት መጠበቅ/..... Error! Bookmark not defined.

1. ሰነ ስርአት መጠበቅ 2

1.1. ሰነስርአትን መጠበቅ 2

1.1.2 ሰነ ስርአት መጠበቅን የሚያሳዩ ዋና ዋና ባህሪያት .. 4

1.1.3 ሰነ ስርአትን የመጠበቅ አሰፈላነት 5

1.1.4.ሰነ ስርአት አጠባበቅን ለማሻሻል የሚረዱ መንገዶች 8

1.1.5 እራስን ከአካላዊ እና ከስነልቦናዊ ጎጂ ተግባራት መጠበቅ 8

1.1.6. ሰነ ሰርአትን መጠበቅ አለመቻል የሚያሰከተለዉ መዘዞች .....Error! Bookmark not defined.

ምዕራፍ ሁለት..... 13

የልጆች ስነ-ስርዓት በቤተሰብ ውስጥ..... 14

2.1. የቤተሰብ ትርጉም..... 14

2.2. የቤተሰብ አባላት አስፈላጊነት..... 15

2.3. በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ያሉ ግብረ-ገባዊ እሴቶች እና መርሆዎች.....Error! Bookmark not defined.
2.4. አወንታዊ የቤተሰብ ግንኙነት..... 19
ምዕራፍ ሶስት..... 22
ጉርብትና 23
3.1. የጉርብትና ትርጉም..... 23
3.2. የጥሩ ጎረቤቶች ባህሪያት..... 25
3.3. የጥሩ ጎረቤቶች አስፈላጊነት..... 27
3.4. ከጎረቤቶች ጋር የሚኖረን አወንታዊ ግንኙነት..... 29
ምዕራፍ አራት .....Error! Bookmark not defined.
የተማሪዎች የትምህርት ቤት ስነስርዓት 34
4.1 የተማሪዎች የትምህርት ቤት ስነስርዓት 35
4.2 የትምህርት ቤት ደንቦች እና መመሪያዎች 36
4.4 ንቁ ተሳትፎ በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት 44
ምዕራፍ አምስት..... 48
የማህበረሰብ እሴቶችን ማወቅ 49
5.1 የማህበረሰብ ትርጉም 49
5.2 የማህበረሰብ እሴቶች..... 53
5.2.1 የማህበረሰብ እሴቶች ትርጉም..... 54

5.2.2 ዋና የማህበረሰብ እሴቶች 54
5.2.2.1. ትብብር 55
5.2.2.2. መቻቻል 56
5.2.2.3.ማካተት/አካታችነት/..... 57
5.2.2.4.ትርጉምያለው ተሳትፎ 58
5.2.2.5.አክብሮት 59
5.2.2.6.እንግዳተቀባይነት 60
5.2.2.7.ታማኝነት 61
5.2.2.8. የለሎችሰዎች ሃሰብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን ... 62
5.2.2.9. ተስፋ 63
5.3 የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊነት 64
ምዕራፍ ስድስት 69
የአካባቢ ባህሎችን ማወቅ 69
6.1 የባህል ጽነሰ ሀሳብ ፍቺ 69
6.2 የአካባቢያዊ ባህል ትርጉም 71
6.3 የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች 72
6.4 የአካባቢያዊ ባህል አስፈላጊነት 74
6.5 የማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች 77

መግቢያ

የሰው ልጅ ምክኒያታዊ እንስሳ መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ሲወዳደር ልዩነቱ ባህሪን የማዳበር ችሎታው ነው። ባህሪ ሰዎች እራሳቸውን ፍፁም እስኪያደርጉ እና ለራሳቸው ያቀዱትን አላማ እስኪያሳኩ ድረስ የሚገነቡት ነው። በተለይም ባህሪን ለማዳበር የሰው ልጆች በምክንያታዊነት እና በግብረ-ገባዊ መርሆች የታነጹ የድርጊት መርሆች ሊኖራቸው ይገባል። ባህሪ ሌሎችን በመምሰል ሊገነባ አይችልም። ምክንያቱም የባህሪ ግንባታ የሰው ልጅ በራሱ አስተሳሰብ የሚመራ ነው በሚለው እሳቤ ላይ ይመሰረታል። ስለዚህ የሰው ልጅ በምድር ላይ ካለ ሌሎች ፍጥረታት ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነት ህሊና ያለውና በምክንያታዊነት የሚያምን መሆኑ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ባህሪን እንዲያዳብር የሚያስችለው ይህአስተሳሰብ ነው። የሰው ልጆች ቀጣይ ትውልዳቸው በማህበረሰብ ውስጥ መኖር እንዲችሉ መመሪያዎችን፣ ስልጠናዎችን እና ትምህርቶችን መስጠት የሚችሉ ብቸኞቹ ምክኒያታዊ እንሰሳት ናቸው። የሰው ልጅ ባህሪያት እና ሌሎች ችሎታዎች በተፈጥሮ የሚወረሱ ሳይሆኑ በትምህርት እና በልምምድ የሚገኙ ናቸው። የሰው ልጆች የመማር ችሎታ በጣም አስፈላጊ ባህሪ

ነው፡፡ ይህ ባህሪ እድገታቸውን እንዲቀጥሉ እና ግብረ-ገባዊ የመሆን ግባቸውን ለማሳካት ያስችላቸዋል፡፡ምንም እንኳን የሰው ልጅች በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች እና ማህበራዊ ባህሪያት የሰለጠኑ ቢሆኑም በሚጠበቀው ልክ ግብረ-ገባዊ አይደሉም፡፡ የሰው ልጅች መልካም ለመሆን መማር አለባቸው የሚለው ድምዳሜ ላይ የተደረሰው ለዚህ ነው።

በዚህ መሰረት መልካም ባህሪ ከመወለድ ጀምሮ እንዳለ ሆኖ ያለ ነገር አይደለም። ከዚህ ይልቅ የሰው ልጅች ሞራላዊ ግዴታን የመወጣት አቅም ያላቸው እንደመሆናቸው፤ መልካምነት በተፈጥሮ ሳይሆን በመማር ሊገኝ ወይም ሊደረስበት የሚገባ ነገር ነው፡፡ የሰው ልጅ መልካም ባህሪን ለማዳበር በሚያደርገው ጥረት ግብረ-ገባዊ ድርጊቶችን በተደጋጋሚ መለማመድን ይጠይቃል፡፡ የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውምና ይህም የሰው ልጅች ሥነ ምግባራዊ ፍጡራን መሆናቸውን የግድ አስፈላጊ ያደርገዋል።

በሌላ አነጋገር ግብረገባዊነት ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና ባህሪ ጋር የተቆራኘ ማህበራዊ ተግባር ነው። በአለም ውስጥ ብቸኛው ሰው ብትሆን፤ ግብረ-ገብነት አይኖርም ነበር።

ምዕራፍ አንድ

የራስን ሰነ ስርአት መጠበቅ

ከዚህ ምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፤

- ሰነ ስርአትን መጠበቅን የሚያሳዩ ቁልፍ ባህሪያትን ታብራራላችሁ፤
- ሰነስርአትን የመጠበቅ አሰፈላጊነትን ግምት ውስጥ ታስገባላችሁ፤
- ራስን ከአካላዊና ስነ ልቦናዊ እንዲሁም ከጎጂ ልማዶች ለመጠበቅ የሚረዱ ድርጊቶችን ታሳያላችሁ፤
- ሰነ ስርአትን አለማክበር የሚያስከትለውን ጉዳቶች ትለያላችሁ፤

1.የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ

1.1. የራስን ስነስርአት መጠበቅ ምንነት

ውድ ተማሪዎች፣ የራስን ስነ ስርአት የመጠበቅ ምንነትን ታውቃላችሁ?

እባካችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ መልሳችሁን ተናገሩ።

የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ ማለት ጥሩ ጠባይ ማሳየት ማለት ነው። ለምሳሌ ለወላጆች፣ለሌሎች የቤተሰብ አባላት እና ለጎረቤቶች የምናሰየዉ መልካም ባህሪይ ነዉ።

ስነ ስርአትን መጠበቅ መልካምና እና ተወዳጅ ልጆች የሚያሳዩት ጥሩ እና ተቀባይነት ያለው ጠባይ ነው። የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ የሚከተሉትን ምሳሌዎችን ያካትታል።

- ☞ወላጆችን እና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን ማክበር
- ☞ለወላጆች እና ለትላላቅ ሰዎች ክብር መሰጠት
- ☞ለወላጆች እና ለሌሎች የቤተሰብ አባላት መታዘዝ
- ☞በትምህርት ቤት ዉሰጥ መምህራን ፤ርዕሳነ መምህራን እና ሌሎች የማህበረሰብ አካላትን ማክበር
- ☞ጤናማ ለመሆን የግል ንፅህናን መጠበቅ
- ☞የተስተካከለ እድገት እንዲኖራችሁ በበቂ ሁኔታ ሰአትን ጠብቆ መመገብ፣
- ☞ ባቅማችሁ መጠን ቤተሰቦቻችሁን በስራ ማገዝ መርዳት

☞ጨዋታዎችን ከጓደኞቻችሁ ጋር ደህንነታቸው በተጠበቁ ቦታዎች መጫወት፣ ወዘተ...



ምስል 1. የራስን ስነ ስርአት የሚጠብቁ ልጆች የሚያደርጓቸዉ ተግባራት

1.2 የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ ዋና ዋና ባህሪያት

ውድ ተማሪዎች፣ እባካችሁ ሁል ጊዜ አስታውሱ ስነ ስርአትን የሚጠብቅ ሰው የሚከተሉት ባህሪያት አሉት/ያሳያል ።

- የስነ-ስርአት ደንቦችን ለማወቅና ለመተግበር በጣም ይጓጓል፤
- ለቤተሰብ ሁልጊዜ በቅንነት ይታዘዛል፤
- ለቤተሰብ እና ለጎረቤት ይታዘዛል፤
- በየቀኑ የራስ ስነ ስርአትን ለመጠበቅ ይሞክራል፤
- ትክክል ያለሆነ ነገር በሚገጥምበት ጊዜ ወላጆችን ለመጠየቅ ድፍረት ይኖረዋል፤
- የራሱን ስነ ስርአት ለመጠበቅ የሌላ ሰው ጥያቄ አያስፈልገውም፤
- ከቤተሰብ አባላት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ይኖረዋል፤
- በአካባቢው ውስጥ ሰላማዊ ግንኙነት ይኖረዋል፤
- በትምህርት ቤት ውስጥ ታታሪ ተማሪ በመሆን ይታወቃል።።



ምስል 2. የራስን ስነ ስርአት የሚጠብቁ ልጆች የሚያሳዩት ባህሪያት

1.3 የራስን ስነ ስርአት የመጠበቅ አስፈላጊነት

ውድ ተማሪዎች ስነ ስርአትን መጠበቅ ለብዙ ምክንያቶች አስፈላጊ ባህርይ ነው።።ይህ ባህርይ ለራሰ እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ጠቃሚ ነው። ስነ ስርአትን መጠበቅ ለጥሩ የቤተሰብ ሕይወት እና ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው።

የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ የሚያስፈልገው ፡-

☞ከተለያዩ አደጋዎች ራስን ለመጠበቅ፤

- በቤተሰብ እና በጎረቤት ዉሰጥ ሰዉ አክባሪ እና ታዛዥ ለመሆን፤
- ለቤተሰብ፣ ለአካባቢ ብሎም ለሀገር መልካም ዜጋ ለመሆን፤
- ቤተሰብ የሚሰጡንን ተግባራት በአግባቡ ለማከናወን፤
- ጠንካራ የሀገር ተረካቢ ዜጋ ለመሆን፤
- ሀላፊነት የሚሰማዉ እና ጥሩ ዜጋ ለመሆን፤
- ለማህበረሰቡ ጠቃም አባል ለመሆን፤
- ጥሩ እና ስኬታማ ተማሪ ለመሆን
- በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት
- የተለያዩ ሽልማቶች ለማግኘት
- ለጓደኞቻችሁጥጥሩ ምሳሌ /አርአያ/ ለመሆን ወዘተ...ናቸዉ፡፡



ምስል 3፡ /ውጤታማ ተማሪዋ ተግባሯን ለማከናወን ስታስብ



ምስል 4፤ የራሱን ሰነሰርአት የሚጠብቅ ተማሪ ሽልማት ሲያገኙ

1.4. የራስን ስነስርአት አጠባበቅ ለማሻሻል የሚረዱ መንገዶች

ውድ ተማሪዎች፣ ሰነ ስርአት መጠበቅ መልካም እና አስፈላጊ ባህሪ ስለሆነ በተለያዩ መንገዶች ሊሻሻል ይችላል ለምሳሌ፡-

- ☞የራስን ሰነ ስርአት መጠበቅን ለማሻሻል ያለማቋረጥ ጥረት ማድረግ
- ☞ዘወትር የወላጆቻችንን ምክር በመስማት
- ☞ለጓደኞቻቸዉ አርአያ ለመሆን ጥረት በማድረግ
- ☞የጥሩ አርአያ ምሳሌ የሆኑ ሰዎችን ተግባር በመቅሰም
- ☞በቤተ እምነቶች የሚሠጡ የመልካም ስነምግባር መገለጫ ትምህርቶችን መከታተል



ምስል5፡-ሰነ ስርአትን የሚጠብቁ ልጆች እርስ በርሳቸዉ ሰረዳዱ

1.5 እራስን ከአካላዊ እና ስነልቦናዊ ጎጂ ተግባራት መጠበቅ

ውድ ተማሪዎች ካልተጠነቀቅን እና የራሳችንን ሰነ ስርአት መጠበቅ ካልቻልን የተለያዩ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ችግሮች ሊያጋጥሙን ይችላሉ።

ለዚህም የሚከተሉት ሁለት ታሪኮች ያነሳነዉን ሀሳብ ግልጽ ያደርጋሉ።፡

ታሪክ-1. ሀዋ እና ስንታየሁ በሰልጤ ከተማ የሚኖሩ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ጓደኛሞች ናቸው። አንድ ቀን ወላጆቻቸው ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ በሄዱበት ከቤት ውስጥ በጣም ብዙ ስኳር ሰረቁ። ትንሽ ቆይተዉ ፣ ስኳር አብዝተው ስለበሉ ሁለቱም ይታመማሉ እና ማስመለስ ይጀምራሉ። ወላጆቻቸው ሲመለሱ እና ጉዳዩን ሲሰሙ ስንታየሁ እና ሀዋ አብረው ላለመጫወት ለአንድ ሳምንት ተቀጡ፤ በዚህ ጊዜ ሁለቱም ደስ የማይል የብቸኝነት ስሜት ተሰማቸዉ።

ታሪክ-2. ሴና እና አሊሚራህ አርባምንጭ ከተማ የሚኖሩ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። አንድ ቀን ለወላጆቻቸዉ የተዘጋጀውን ቅባት የበዛበት ምግብ በድብቅ ይበላሉ። በዚህ ምክንያት ሁለቱም ቀኑን ሙሉ የህመም ስሜት ሲሰማቸዉ በመዋሉ በወላጆቻቸውም ሊቀጡ ችለዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ታሪኮች ላይ እንዳነበባችሁት ሰነ ስርአት ስርአታችሁን መጠበቅ ካልቻላችሁ የተለያዩ ስነልቦናዊ እና አካላዊ ችግሮች ያጋጥሟችኋል፤ ስለዚህ ሁል ጊዜ እራሳቸሁን ከተለያዩ ጎጂ ተግባራት መጠበቅ አለባችሁ።

1.6. የራስን ስርአት አለመጠበቅ የሚያሰከተለዉ ጉዳት

ውድ ተማሪዎች የራስን ሰነ ሰርአት የመጠበቅ ባህሪን ማዳበር ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ከዚህ ቀደም ተምራችኋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ አለመቻል ደግሞ የሚከተሉትን ጉዳቶች ያሰከትላል፡፡

- ለተለያዩ አካላዊ አደጋዎች ያጋልጣል፤ ለምሳሌ የእሳት ቃጠሎ፣የኤሌክትሪክ ንዝረት ወዘተ
- በጎረቤት ዘንድ እንደ ጥሩ ልጅ አለመቆጠር/አለመታየት
- አብረው የሚጫወቱ መልካም ጓደኞችን ማጣት
- በጎረቤት ዘንድ መጥፎ ሰም መስጠት
- በጎረቤት ዘንድ ወዳጃዊ ስሜት ማጣት
- ወላጆች በልጆቻቸዉ መከፋት
- በቤተሰብ አባላት ውስጥ ተገቢዉን ክብር አለማግኘት
- ብቸኛ ልጅ መሆን/የብቸኝነት ሰሜት / ወዘተ ...



ምስል 6፡-አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ የልጆች ድርጊቶች

ምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

የራስን ሰነ ስርአት መጠበቅ ማለት በአንድ ሰው ላይ የሚታይ መልካም ባህሪይ ማለት ነው፤

የራሱን ሰነ ስርአት የሚጠበቅ ሰው የሰነ ሰርአት ህጎችን ማክበር፣ሰላማዊ፣ ቤተሰብን ማክበር፣ ከፍተኛ የመማር ፍላጎት ወዘተ የመሰለ ባህሪዎችን ያሳያል።

ስነ ስርአትን መጠበቅ ለጥሩ የቤተሰብ ሕይወት እና ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ አስፈላጊ ባህርይ ነው። ስነ ስርአትን መጠበቅ አለመቻል አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳቶችን ያስከትላል።

የምዕራፍ አንድ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡ አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት ብላችሁ መልስ ስጡ።

1.የራስን ስነ ስርአት ለመጠበቅ ሁልጊዜ ለሌሎች ሰዎች ልንታዘዝ ይገባል።

2. የቤተሰብ አባላትን ማክበር ስነ ስርአትን የመጠበቅ አካል ነው።

3. የራስን ስነ ስርአት መጠበቅ ጎጂ ተግባር ነዉ።

4. ሃይማኖታዊ የሆኑ መጻሕፍትን ማንበብ ስነ ስርአት መጠበቅን ለማሻሻል ይረዳሉ፡፡

5.የራስ ስነ ስርአት መጠበቅን ለማሻሻል ዘወትር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

የልጆች ስነ-ስርዓት በቤተሰብ ውስጥ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፤

- ቤተሰብ የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- የቤተሰብ አባላትን አስፈላጊነት ታብራራላችሁ፡፡
- በቤተሰብ ውስጥ የሚተገበሩ የግብረ-ገብ እሴቶችን እና መርሆዎችን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ከቤተሰቦቻችሁ ጋር የሚኖራችሁን የአዎንታዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት ታደንቃላችሁ።
- በቤተሰብ መካከል በሚኖረው አዎንታዊ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ለይታችሁ ታወቃላችሁ።

2.1. የቤተሰብ ምንነት

ውድ ተማሪዎች፣ የቤተሰብ ጽንሰ-ሀሳብ በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎም ይችላል። ለምሳሌ ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ዉስጥ የሚኖሩ የሰዎች ስብስብ ማለት ነዉ፡፡

ቤተሰብ ማለት ወላጆች፣ ልጆች እና ዘመዶችን የሚያቅፍ የማህበረሰብ መሰረታዊና የመጀመሪያ ደረጃ ክፍል ማለት

ነው። ቤተሰብ እንደ አባት፣ እናት ፣ ልጆች፣ አክስቶች ፣ አጎቶች፤አጋሮች/የቤት ዉስጥ ሰራተኞች እና የሌሎች ግለሰቦች ስብስብ ተብሎ ሊገለጽም ይችላል።



ምስል 7፡- ፋጡማ በወላይታ ሶዶ ከተማ የሚኖሩ አያቶቿን ስትጎበኝ

2.2. የቤተሰብ አባላት አስፈላጊነት.

ውድ ተማሪዎች ከላይ እንዳነበባችሁት እና በምስሉ ላይ እንዳያችሁት አንድ ቤተሰብ የተለያዩ አባላት አሉት፡፡

ሁሉም የአንድ ቤተሰብ አባላት እንደየ እድሜያቸው የራሳቸው የስራ ድርሻ እና ሚና አላቸው።።

<u>እናት፡</u> እናት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ካሉ የቤተሰብ መሪዎች አንዷ ናት፤ እናቶች የወላጅነት፣የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ሚናዎችንም ይወጣሉ።

<u>አባት፡</u> አባት በቤተሰብ ውስጥ ያለ ሌላኛው መሪ ነው። አባቶችም እንደ እናቶች ሁሉ የወላጅነት ፣የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ሚናዎችን ፖምር ይወጣሉ።

<u>ወንድ ልጆች፡</u> ወንድ ልጆች ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዱ ናቸው ። እንደደረሱበት የእድሜ ደረጃ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ እንዲሁም ወላጆቻቸውን፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን እና ጎረቤቶቻቸውን እነዲረዱ ይጠበቅባቸዋል።።

<u>ሴት ልጆች፡</u> ሴት ልጆች፡ ሌለኞቹ የቤተሰብ አባላት ናቸው። ከወንድ ልጆች በተመሳሳይ ሴት ልጆችም እንደደረሱበት የእድሜ ደረጃ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ እንዲሁም ወላጆቻቸውን፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን እና ጎረቤቶችን እነዲረዱ ይጠበቅባቸዋል፤

አጎቶች፣ አክስቶች እና ሌሎች የቅርብ የቤተሰብ አባላትም በቤተሰብ ውስጥ የየራሳቸው የስራ ድርሻና እንደ ሁለተኛ ወላጅነት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሚናዎች አሏቸው። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር ስለሆነ

በክፉም በደጉም ጊዜ መደጋገፍ ስላለበት ሁሉም የቤተሰብ አባላት ለሁላችንም በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

ታሪክ1. ዮሐንስ በሆሳእና ከተማ በሚገኝ የእውቀት ጮራ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው። ሁለቱም ወላጆቹ እየሰሩ የልጆቻቸውን ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ሰለሚያሟሉ ምንም የሚያስጨንቀው ነገር የለም፤ስለሆነም ሙሉ ትኩረቱን ትምህርቱ ላይ ያደርጋል።

ታሪክ 2. ፋጡማ የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ተማሪ ነች። በመጪው ክረምት በዲላ ከተማ የሚኖሩትን አያቶቿን ልትጎበኝ ትሄዳለች። ይህን የምታደርገው አጎቶቿ እና አክስቶቿ የመጓጓዣ ወጪዋን ለመሸፈን ስለተስማሙ ነው።
ለማጠቃለል ሁሉም የቤተሰብ አባላት በመልካም እና በአስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ አስፈላጊ ናቸው።

2.3. በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ግብረ-ገባዊ እሴቶች እና መርሆች

ውድ ተማሪዎች፣ ግብረገባዊ እሴቶች እና መርሆች ድርጊቶቻችንና ባህሪያችን ጥሩ እና ተቀባይነት ያለው እንዲሆኑ ሊያድርጉ የሚችሉ ህጎች ናቸው።

ሁሉም ቤተሰቦች ሰላማዊ እንዲሆኑና በአግባቡ እንደ ቤተሰብ እንዲቀጥሉ መከተል ያለባቸው ግብረ-ገባዊ እሴቶች እና መርሆዎች አሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ☞በቤተሰብ አባላት መካከል መከባበር መኖር
- ☞በቤተሰብ አባላት መካከል ትብብር መኖር
- ☞በሚናገሩትና በሚያደርጉት ሁሉ ፈጣሪን መፍራት
- ☞የቤተሰብን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መረዳትና እንደ ቤት መኖር
- ☞የቤተሰቡን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማሳደግ ወላጆችን በአቅም ልክ ማገዝ

በአጠቃላይ እነዚህን ግብረ-ገባዊ እሴቶች እና መርሆዎች የሚያከብር ቤተሰብ ስኬታማ እና ጤናማ ቤተሰብ እንደሚሆን ይታመናል ::



ምስል 8፡- ግብረ-ገባዊ እሴቶች እና መርሆችን የሚያከብር ቤተሰብ

2.4. አወንታዊ የቤተሰብ ግንኙነት

በማንኛውም ቤተሰብ አባላት ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነት መኖር በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ በቤተሰብ አባላት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖር ጥሩ ስነምግባር ያላቸውና የሚከባበሩ ወላጆች እና ልጆች ሊኖሩ ይገባል፡፡

ቴዎድሮስ፣ እህቱ ትግስት እና ወላጆቻቸው በጅንካ ከተማ ይኖራሉ፡፡ ወላጆቻቸው የልጆቻቸውን መሠረታዊ ፍላጎቶች ያሟላሉ፡፡ ልጆቹ ወላጆቻቸውን በማክበር በቤት ውስጥ ስራ

ይረዷቸዋል፡፡ ስለዚህ የእነርሱ ቤተሰብ አዎንታዊ ግንኙነት ያለው ቤተሰብ ነው።

በቤተሰብ መካከል በሚኖረው አዎንታዊ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች፡-

ውድ ተማሪዎች፣ ቤተሰብ የሀገር መሰረት ነው። ስለዚህ አዎንታዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር በደንብ ሊጠበቅ እና ሊመራ ይገባል፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በቤተሰብ መካከል በሚኖረው አዎንታዊ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች አለ፡፡እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ልጆቻቸዉን በተገቢዉ መንገድ የማያሳድጉ ወላጆች
- ስነ ስርአት የሌላቸዉ ልጆች
- የውጭ ባህላዊ ተጽእኖ
- ሀላፊነታቸዉን በአግባቡ የማይወጡ ሀይማኖታዊ እና ሌሎችም ተቋማት ወዘተ ናቸዉ፡፡

የምእራፉ ሁለት ማጠቃለያ

- ቤተሰብ ማለት ዝምድና ያላቸው የሰዎች ስብስብ ነው።
- ሁሉም የቤተሰብ አባላት በመልካምም ሆነ በአስቸጋሪ ጊዜያት በጣም አስፈላጊ ናቸው።
- የቤተሰብ እሴቶች በቤተሰብ ውስጥ ወላጆችን ማክበርን፣ እርስ በእርስ መረዳዳትን ወዘተ ያካትታሉ።
- በቤተሰብ ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነት ሲኖረን በኢኮኖሚ ፣ በስነ-ልቦና ፣ ወዘተ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን።
- በቤተሰብ ውስጥ ጥሩ ግንኙነት ከሌለን የተለያዩ ችግሮች ሊከሰቱብን ይችላሉ።

ምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ እውነት፤ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ ፡፡

1. ቤተሰብ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ካሉ ማህበራዊ ተቋማት አንዱ ነው ፡፡
2. ቤተሰብ ለመልካም ጊዜ ብቻ የሚያስፈለግ ተቋም ነዉ፡፡
3. ወላጆችን መርዳት የቤተሰብ ግብረ-ገባዊ መርህ ነው።
4. በቤተሰብ መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩ አስፈላጊ ነው።
5. በቤተሰብ ውስጥ ያሉ አዎንታዊ ግንኙነቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሊጎዱ ይችላሉ።

ምዕራፍ ሶስት

ጉርብትና

ከምዕራፍ የሚጠበቁ አጥጋብ የመማር ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተመራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።

- **የጎረቤትን ትርጉም ትገልጻላችሁ፤**
- **የጥሩ ጎረቤት አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ ታሰገባለችሁ፤**
- **የመልካም ጎረቤቶችን ባህሪያት ታሳያላችሁ፤**
- **ጥሩ ጎረቤቶችን ለመገንባት የመልካም ተግባቦት ሚናን ትገልጻላችሁ፤**
- **በጉርብትና ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶችን ትለያላችሁ፤**

3.1. የጉርብትና ምንነት

ውድ ተማሪዎች፣ ጉርብትናን ለመግለጽ የጎረቤትን ትርጉም ማወቅ አለባችሁ።

ጎረቤት የምንለው ከቤታችን አጠገብ የሚኖር ቤተሰብ ነው።

አንዱ ቤተሰብ ከሌላኛዉ ቤተሰብ ጋር በጋራ ተግባበተዉ ፣ ተባበረዉ እና ተረዳድተዉ ሲኖሩ ጉርብትና ተብሎ ይጠራል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ጠንካራ የጉርብትና ባህል አለን። በመልካም እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እርስ በእርሳችን እንረዳዳለን። ወላጆቻችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በደህንነት ጉዳዮች በጥበብ እርስ በርሳቸዉ ይደጋገፋሉ።

ልጆች የተለያዩ ዕቃዎችን ለመግዛት ወደ ገበያ ወይም ሱቅ በመሄድ ለጎረቤቶቻቸው በመላክና ከልጆች ጋር አብረው በመጫወት ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ።።

ውድ ተማሪዎች፣ እባካችሁ ከጎረቤቶቻችሁ ጋር ያላችሁን መልካም ግንኙነት ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ሽምሱ እና ጎረቤቶቹ

ሽምሱ በወልቂጤ ከተማ የሚኖር የ7 አመት የ1ኛ ክፍል ተማሪ ነው። ሽምሱ ሰነ ሰርአት ያለዉ እና ከጎረቤቶቹ ጋር መልካም ጉርብትና ያለዉ ልጅ ነው። እማማ ፀሃይ ከነ ሽምሱ ቤት በስተግራ በኩል ይኖራሉ። እማማ ፀሀይ አሮጊት ስለሆኑ ሽምሱ ውሃ በማምጣት እና በአቅራቢያው በሚገኝ ሱቅ ዕቃዎችን በመግዛት ይረዳቸዋል። ከነ ሽምሱ ቤት በስተቀኝ በኩል ደግሞ የአስቴር ቤተሰብ ይኖራሉ። አስቴር የ7 አመት

ልጅ ስለሆነች ከጥናት በኋላ ከሸምሱ ጋር አብረዉ ይጫወታለ፤ ስለሆነም ጎረቤቶች በሰላም እና በስምምነት አብረዉ ይኖራለ። ጉርብትና የሚባለው እንግዲህ ይህ ነው።

3.2. የመልካም ጎረቤቶች ባህሪያት

ውድ ተማሪዎች ጉርብትና ጠቃሚ እና አስፈላጊ ማህበራዊ እሴት ነው። እናም ጥሩ ጎረቤት መኖሩ ለማህበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ ግቦቻችን መሳካት ወሳኝ ሚና ሊኖራቸዉ ይችላለ፤መልካም ጉርብትና መመሰረት ወሳኝ እና አሰፈላጊ ነዉ። በመሆኑም መልካም ጎረቤት መኖር ለብዙ ነገሮች አሰፈላጊ ነው።

መልካም ጎረቤቶች የሚከተሉት ባሕርያት አላቸዉ።

- ✓ በመልካም ሆነ በችግር ጊዜ ሰዉን የሚቀበሉና እና የሚቀርቡ ናቸው።
- ✓ ሁል ጊዜ ለጎረቤቶቻቸው ክብር ይሰጣለ።
- ✓ የጎረቤቶቻቸውን መብት በማክበር አብሮ በሰላም ይኖራለ።
- ✓ የጎረቤቶቻቸውን ጸጥታ አያዉኩም። ወይም የድምፅ መረበሽን ያስወግዳለ።

- ✓ አካባቢው ለመኖር ጤናማ እና ምቹ እንዲሆን የአካባቢን ንጽህና ይጠብቃሉ።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎች የመልካም ጎረቤቶች ባህሪያት መኖር ማህበራዊ ህይወታችን ስኬታማ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።



ምስል 9፡- ጎረቤታሞች አካባቢያቸውን በጋራ ሆነዉ ሲያጸዱ



ምስል 10፡- የመልካም ጉርብትና መገለጫዎች

3.3. የመልካም ጎረቤት አስፈላጊነት

ውድ ተማሪዎች እባካችሁ ሁሌም የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ መሆኑን አስታውሱ። ሰለዚህ የሰው ልጅ ማህበራዊ እንስሳ በመሆኑ ተባብሮ ፣ተረዳድቶና ተደጋግፎ እንዲኖር መልካም ጎረቤት ያሰፈልገዋል።አንድ ሰው ብቻውን ለረጅም ጊዜ መቆየት አይችልም። ሰለዚህ አብረዉ ልኖሩ የሚችሉ መልካም ጎረቤቶች ያሰፈለጉታል። ቤተሰቦቻችን ለእኛ አስፈላጊ እንደመሆናቸው መጠን ፣ ጎረቤቶቻችንም ደግሞ ለሁላችንም አስፈላጊ ናቸው። ጎረቤቶቻችን ለክፉም ለደጉም መኖራቸው አሰፈላጊ ናቸው።ለብዙ ማህበራዊ እና

ኢኮኖሚያዊ አላማችን መሳካት ጥሩ ጎረቤቶች ወሳኝ ሚና አላቸው።

የሚከተሉት ከመልካም ጎረቤት አስፈላጊነት መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ፡-

- መልካም ጎረቤቶች ለትክክለኛ ማህበራዊ እድገታችን የሚረዱ ምክሮችን ይሰጡናል።
- ቤተሰባችን በተለያዩ ማህበራዊ እና ከስራ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች በማይኖሩበት ጊዜ ጎረቤቶች ተካተዉ ይሳተፋለ።
- አብረው የሚጫወቱ እና የሚያድጉ ጓደኞችን ይሰጣል።
- ቤተሰቦቻችንን ለገጠማቸዉ ችግሮች መፍትሄ/ምክር ይሰጣለ።
- ለወላጆች ልጆቻቸውን የሚያሰተምሩበት ጥሩ ትምህርት ቤቶችን ፣ የሚያሳክሙበት ጥሩ ሆስፒታሎች እና ለልጆቻቸው የሚያስፈልጉ የሥራ ዕድሎችን መረጃ ይሰጣለ።
- ማህበራዊ ህይወታችን ስኬታማ እንዲሆን ያግዙናል።

3.4. ከጎረቤት ጋር የሚኖረን አዎንታዊ ግንኙነት

ሰላማዊ ግንኙነት መመሥረት ለኑሯችን አስፈላጊ ነው። ከጎረቤቶቻችን እና ከሰዎች ሁሉ ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖረን የሚከተሉትን የተግባቦት ክህሎቶች ሊኖረን ይገባል። እነዚህም፡-

- ☞ጥሩ የተግባቦት ክህሎት
- ☞የሌሎችን ስሜት በአግባቡ መረዳት
- ☞ለሌሎች ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ
- ☞የሌሎችን አመለካከት መረዳት
- ☞ሌሎች እርዳታ በሚያሰፈልጋቸዉ ጊዜ መርዳት
- ☞ታማኝ እና በራሱ ችሎታ የሚያምን ሰው መሆን
- ☞የሌሎችን ሀሳብ በአግባቡ ማዳመጥ
- ☞ ተባብሮ በመስራት ማመን
- ☞ችግርን የመፍታት ክህሎት መኖር
- ☞ጠቃም አስተያየት መስጠት፣ ወዘተ...

ከላይ የተጠቀሱትን የተግባቦት ክህሎቶችን በማዳበር ከጎረቤቶቻችን ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረን እና ህይወታችንን የበለጠ ደስተኛ ማድረግ እንችላለን።



ምስል 11፡- የሚግባቡ ልጆች አብረው እግር ኳስ ሲጫወቱ

3.5. በጉርብትና ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ነገሮች

ውድ ተማሪዎች፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረን የተግባቦት ክህሎቶች እንደሚያስፈልጉ ከዚህ ቀደም አይታችኋል። በሚቀጥለው የምትማሩት በጉርብትና ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ነገሮችን ይሆናል።

እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡-

- ✓ ከሚያመሳስሉ ነገሮች ይልቅ በልዩነት ላይ ማተኮር
- ✓ /ግለኝነት/ብቸኝነት /
- ✓ አደንዛዥ ዕፅ እና አልኮል መጠቀም

✓ ወዳጃዊ/ /ስሜት አለመኖር

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ በሰዎች ጉርብትና ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉት ምክንያቶች በመሆናቸዉ ልናስወግዳቸዉ ይገባል፡፡



ምስል11፡- አለመስማማት ወደ አለመግባባት ሰያመራ

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

ጎረቤት ማለት ከቤታችን አጠገብ የሚኖር ቤተሰብ ማለት ነው። ጎረቤቶች ከቤተሰባችን አባላት ቀጥሎ ለእኛ አስፈላጊ ናቸው፤ጥሩ ጎረቤቶች እርስ በርሳቸዉ ይከባበራሉ ይረዳዳሉ ዋጋም ይሰጣጣሉ።።

ጎረቤቶች ጥሩ ግንኙነት ሊኖራቸው የምችለዉ ጥሩ የተግባቦት ክህሎት ካላቸዉ ብቻ ነዉ፤ግለኝነት፣ ስነ-ስርአት መጠበቅ አለመቻል እና የውጭ ባህል ተጽእኖ መኖር በጉርብትና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. ጉርብትና እና ጎረቤት ተመሳሳይ ሀሳቦች ናቸው።

2. ማህበራዊ ትብብር የመልካም ጉርብትና ባህሪ ነው።

3. በመልካምም ሆነ በችግር ጊዜ ጎረቤቶች ያስፈለጋሉ።

4. ጥሩ የተግባቦት ክህሎት መኖር ለጉርብትና ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ መስፈርቶች አንዱ ነው።

5. ግለኝነት ጉርብትና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

ምእራፍ አራት

የተማሪዎች የትምህርት ቤት ስነስርዓት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምእራፍ ከተማራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፡-

- **የተማሪዎች የትምህርት ቤት ስነስርዓት ምን ማለት እንደሆነ ታብራላችሁ፤**
- **የትምህርት ቤት መመሪያና ደንቦችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ፣**
- **በትምህርት ቤት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የአዎንታዊ ግንኙነት መገለጫዎች ትገልጻላችሁ፤**
- **በትምህርት ቤት ውስጥ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት አስፈላጊነትን ትረዳላችሁ፤**
- **ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር አዎንታዊ ግንኙነትን ታዳብራራችሁ፤**

4.1 የተማሪዎች የትምህርት ቤት ስነስርዓት

ቁልፍ ሐረግ

የክፍል ስነስርዓት



ምስል 11፡- ትምህርታቸውን በአግባቡ የሚከታተሉ ተማሪዎች

ተግባር 1

ተማሪዎች ከላይ ያለውን ምስል ተመልከቱና የተገነዘባችሁትን ለመምህራችሁ ንገሯቸው።።

1. **በስዕል 11 መሰረት የትምህርት ቤት ስነስርዓት ማለት ምንድን ነው?**

የትምህርት ቤት ስነስርዓት ማለት የትምህርት ቤት ደንቦችን እና መመሪያዎችን ማክበርና በመማር - ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሚያሳድሩ ያልተገቡ ባህሪያትን ማስተካከል ማለት ነው።

4.2 የትምህርት ቤት ደንቦች እና መመሪያዎች

ተግባር 2

ተማሪዎች ከታች በስዕል 12 **የሚገኘውን ምስል ተመልከቱ እና**

ምን እንደሚያሳይ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ። ከዚያ መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው።።



ምስል 12፡- ተማሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ብሔራዊ መዝሙር ሲዘምሩ።

አዘውትራችሁ በቡድን የምታከብሯቸውን የትምህርት ቤት መመሪያ እና ደንቦች ለዩና መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው።

በት/ምህርት ቤታችሁ በማሰታወቂያ ሰሌዳ የሚለጠፍ መመሪያ እና ደንቦችን የሚያሳይ ስእል ሳሉና ለመምህራችሁ አሳዩአቸው።።

መዝሙር

"ትምህርት ቤቴ ሁልጊዜም ውብ ነች."

ዛሬ ቃል እገባለሁ የሚቻለኝን ላደርግ አንዳች ሳልሰለች፤

ለደንብ ለህጎቿ ከልቤ ለመገዛት፣

እኔም ድርሻ አለብኝ ለቅጥሯ ሰላማዊነት፤

ለደህንነቴ ባለድርሻ እኔ ነኝ፤ ለመከባበር ፣

ለተሟላ ስኬት ቃል እገባለሁ፤

ትምህርት ቤቴን የዕውቀቴን ማዕድ፣

የመንገዴን መሪ እወዳታለሁ።።

ግጥም

ዘወትር ወደ ክፍሌ በሥርዓት እገባለሁ፣

የዕውቀት አባቴን መምህሬን በአክብሮት ሰላም እላለሁ፣

ጓደኞቼንና መምህራኖቼን በጨዋነት አናግራለሁ፣

መምህር ሲያስተምር በአትኩሮት፣ በጸጥታ አዳምጣለሁ፣

መጫዎቻ ሜዳ እና መጸዳጃ በአግባቡ እጠቀማለሁ።።



ምስል 13፡- በሰልፍ ወደ መማሪያ ክፍላቸው የሚገቡ ተማሪዎች



ምስል14 ፡-መምህር ወደ ክፍል ዉስጥ ሲገባ ተማሪዎች በአክበሮት ሲቀበሉት

ተግባር 3

ከዚህ በታች የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ኃላፊነት የሚሰማው ተማሪ የትምህርት ቤት መመሪያና ደንቦችን ያከብራል።
2. ወደ ክፍል ከመግባታችሁ በፊት ብሔራዊ የህዝብ መዝሙር መዘመር አስፈላጊ አይደለም፡፡
3. በሰዓት ወደ ትምህርት ቤት መምጣት የትምህርት ቤት መመሪያና ደንቦች አንዱ አካል ነው።
4. ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ መጫወቻ ሜዳ ላይ መጫወት ይችላሉ።
5. ተማሪዎች በትምህርት ሰዓት የትምህር ቤቱን የደንብ ልብስ መልበስ የትምህርት ቤት ህግ ነው።

4.2.1 የተማሪዎች መብት እና ኃላፊነት በትምህርት ቤቱ ውስጥ



ምስል 15 ፡-የመማር መብታቸውን እየተጠቀሙ ያሉ ተማሪዎች።

ተግባር 4፡

ከላይ የቀረበውን ስዕል መሰረት በማድረግ ከታች ያሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ጻፉና መልስ በመስጠት መልሳችሁን ለመምህራችሁ አሳዩአቸው፡፡

- ምስሉ ምን ያሳያል?
- ምስሉ ላይ ያሉት ተማሪዎች ምን እየሰሩ ነው?

መዝሙር

ቃልኪዳኔ ለትምህርት ቤቴ

የምችለውን ለማድረግ ቃል እገባለሁ በምወዳት ትምህርት ቤት፤ መብት አለኝ ለመማር ግብረ-ገብ እንዲሁም ሌላ ትምህርት፣ግዴታዬ ደግሞ ለትምህርት ቤቴ ህጎች ለመገዛት፣ ይህ ግዴታዬ ነው እኔም ቃል ገባለሁ፣የትምህርት ቤቴን ግቢ ንጽህናውን እጠብቃለሁ፡እኔም ቃል ገባለሁ፤የደንብ ልብስ በአግባቡ ለብሳለሁ፤እኔም ቃል ገባለሁ ትምህርቴን ሳላቋርጥ እከታተላለሁ።።ይህ ግዴታዬ ነው እኔም ቃል ገባለሁ፣እስክሪቢቶ፣እርሳስ ምንም ሳላጓድል፣ በሙሉ ዝግጅት ክፍል እገባለሁ ይህ ግዴታዬ ነው እኔም ቃል ገባለሁ።።

4.3 አወዎንታዊ ግንኙነት በትምህርት ቤት ውስጥ

ቁልፍ ሐረግ

አዎንታዊ (መልካም) ግንኙነት



ምስል 16 ፡-በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ሲወያዩ

ከላይ ያለውን ምስል ተመልከቱ እና ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

ተግባር 5፡

በስእል 16 ላይ ያለው ምስል ምን ያሳያል?

ቡድን መስርቱና በመካከላችሁ አዎንታዊ ግንኙነቶች መመስረት ስላለው አስፈላጊነት ተወያዩ ፡፡

ተማሪዎች ሰው አክባሪ፣ ደግ ፣ ታማኝ ፣ ተግባቢ ፣ ሩሩህና ደጋፊ ከሆናችሁ፤ ከክፍል ጓደኞቻችሁና ሌሎች በትምህርት

ቤታችሁ ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር አዎንታዊ/ መልካም ግንኙነት መፍጠር ትችላላችሁ።

ተግባር 6

ከላይ በተሰጠው ጽሑፍ ላይ በመመስረት ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ተማሪዎች በመካከላቸው አዎንታዊ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው።
2. ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቻቸውን መደገፍ የለባቸውም።
3. ታማኝነት አዎንታዊ ግንኙነትን ለማዳበር አንዱ መንገድ ነው።
4. እርስ በእርሳችን ስንደማመጥ አዎንታዊ ግንኙነትን እንገነባለን፡፡
5. ደግነት ለአዎንታዊ ግንኙነት ምንም አስተዋፅዖ የለውም።

4.4 ንቁ ተሳትፎ በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት



ምስል17፡-ተማሪዎች በባህላዊ ልብሶች አጊጠዉ የስንደቅ አላማ ቀን ሲያከብሩ

ተማሪዎች፣ ከላይ ያለው ምስል ምን ያሳያል?

በትምህርት ቤት የስፖርት ቡድኖች፣ በሒሳብ፣ በንባብ፣ በመዝሙር እና በተለያዩ የተሰጥኦ ትዕይንቶች የሚደረግ ንቁ ተሳትፎ ተጓዳኝ ትምህርት ይባላል። እነዚህ ተግባራት ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሚከናወኑ ናቸው።

ተግባር 7፡

ከላይ በተሰጠው ጽሑፍ ላይ በመመስረት ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. **በትምህርት ቤት ባለ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ንቁ ተሳታፊ መሆን አስፈላጊ ነው፡፡**
2. **በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት የክፍል ውስጥ ትምህርት አካል ናቸው።**
3. **በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት በትጋት የሚሳተፉ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊዎች ይባላሉ።**
4. **የትምህርት ቤት ተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ከመማሪያ ክፍል ውጪ ይካሄዳሉ፡፡**
5. **በትምህርት ቤት የሒሳብ ክበብ ውስጥ መሳተፍ የትምህርት ቤት ተጓዳኝ ትምህርት ተግባር አይደለም፡፡**

የምህራፍ አራት ማጠቃለያ

- የመማሪያ ክፍል ስነስርዓትን ማክበር ማለት የመማሪያ ክፍል መመሪያ እና ደንቦችን መቀበል ማለት ነው።
- የትምህርት ቤት መመሪያ እና ደንቦች የሚባሉት ሰዓት አክባሪነት፣ዘወትር ንፁህ የደንብ ልብስ መልበስ፣የትምህርት ቤት ንብረቶችን በኃላፊነት ስሜት መጠቀም፣ የኢትዮጵያን ህዝብ በሐራዊ መዝሙር መዘመርና የመሳሰሉት ናቸዉ፡
- ተማሪዎች የመማር መብት አላቸው፤በሌላ በኩል ደግሞ ሰአትን ማክበር፣ ትምህርትን በአግባቡ መከታተል እና የደንብ ልብስን በአግባቡ መልበስን የመሳሰሉ ኃላፊነቶች አሏቸዉ፡፡
- በትምህርት ቤት ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነትን ከሚያጠናክሩ ነገሮች መካከል አክብሮት፣ ደግነት፣ ታማኝነትና ተግባቢነትን ያካትታል፡፡
- በትምህርት ቤት ተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ማለት ተማሪዎችን የሂሳብ፣ የንባብ እና የጥበብ ክበባት ባሉ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ማሳተፍ ማለት ነው።

ምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች

ከላይ በተማራችሁት መሰረት ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህትት ከሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. የትምህርት ቤት ስነስርዓት በትምህርት ቤት ውስጥ ተገቢ ባህሪ እንድናሳይ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡
2. በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ከትምህርት ቤት መመሪያ እና ደንቦች አንዱ ነው።
3. ኃላፊነት የሚሰማው ተማሪ የትምህርት ቤት መመሪያ እና ደንቦችን አይጥስም ።
4. ሰዓት አክባሪነት የተማሪ ሃላፊነት አይደለም።
5. በጥሞና መደማመጥና መግባባት በክፍል ጓደኞች መካከል አዎንታዊ ግንኙነት ለመመስረት ያስችላቸዋል፡፡

ምዕራፍ አምስት

የማህበረሰብ እሴቶችን ማወቅ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋብ የመማር ብቃቶች ፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

- **ማህበረሰብ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ታብራራላችሁ፤**
- **የማህበረሰብ እሴቶችን ጽንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፤**
- **በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ እሴቶች ትለያላችሁ፤**
- **የአዎንታዊ ማህበረሰባዊ እሴቶችን አስፈላጊነት ታደንቃላችሁ፤**
- **ዋና ዋና የማህበረሰብ እሴቶችን ታሳያላችሁ፤**

5.1 የማህበረሰብ ምንነት

አንድ ማህበረሰብ የተለያዩ የቤተሰብ አባላት፣ ጎሳ እና የሃይማኖት ቡድን አባላትን ያካትታል።

ሮባ የሚኖረው በአንድ መንደር ዉስጥ ነው። አባቱ ገበሬ ነው እናቱ ደግሞ የቤት እመቤት ናት ።አንድ ቀን ወላጆቹ የአጎቱ ልጅ ወደሚኖርበት ከተማ ሊወስዱት ቃል ገቡለት። በማግስቱ

በማለዳ ከእንቅልፉ ሲነቃ ቤተሰቦቹ በአውቶብስ ወደ ከተማ ወሰዱት።

አምና የምትኖረው ከአባቷ ፣ ከእናቷ እና ከሁለት ወንድሞቿ ጋር በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ ነው። ወላጆቿ ብዙ የግመሎችና የፍየሎች መንጋ አላቸው።



ምስል 18፡-የገጠር ማህበረሰብ



ምስል 19፡-አርብቶ አደር ማህበረሰብ



ምስል 20፡-የከተማ ማህበረሰብ

ከላይ በተገለጸው ታሪክ መሰርት “እውነት” ወይም “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡

1. ሁሉም ማህበረሰቦች የገጠር ነዋሪዎች ናቸው።

2. ማህበረሰብ የምንለው በተናጠል የሚኖሩ የሰዎች ስብስብ ነው።

3. በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የከተማ ማህበረሰብ ይባላሉ፡፡

4. ገበሬዎች የገጠር ማህበረሰብ ናቸው።

5. የከተማ ማህበረሰብ የአርብቶ አደር ሰዎች የሚኖሩበት ነው።

5.2 ማህበረሰባዊ እሴቶች

ቁልፍ ሐረግ

የማህበረሰብ እሴቶች



ምስል 20፡-የሚዋደዱና የሚከባበሩ ተማሪዎች

ተግባር 3

ተማሪዎች፣ ከላይ ያለውን ምስል በመመልከት ምን እንደተገነዘባችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ።

5.2.1 የማህበረሰብ እሴቶች ምንነት

የማህበረሰብ እሴቶች በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ማህበረሰብ አባላት እርስበእርስ የሚጋሩት እምነት ነው። እነዚህም መቻቻል፣ መተባበር፣ መከባበር፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ ታማኝነት ተስፋ እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

ተግባር 4፡ ከላይ በተገለጹት ጽሑፎች መሰረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት መልሱ።፡

1. የማህበረሰብ እሴቶች በማህበረሰቡ አባላት መካከል የጋራ እምነት ናቸው።

2. አክብሮት ግለሰቦች ከሚከተሏቸው የማህበረሰብ እሴቶች አንዱ ነው።

3. የማህበረሰብ እሴቶች በማህበረሰቡ አባላት መካከል አይጋሩም።

4. መተባበር የማህበረሰብ እሴት አይደለም።

5. መቻቻል ጥሩ የማህበረሰቡ እሴት ምሳሌ ነው።

5.2.2 ዋና የማህበረሰብ እሴቶች

ዋና የማህበረሰብ እሴቶች በአንድ ማህበረሰብ የቆዩና ዋና ዋና እምነቶች እና በጎነቶች ናቸው።

ተግባር 5፡

ከታች ያሉትን ምስሎች በመመልከት እና ራሳችሁን ከእያንዳንዳቸው እና ከሚወክሉት ዋና የማህበረሰብ እሴቶች ጋር በደንብ እንዲተዋወቁ አድርጉ።

5.2.2.1. ትብብር

ትብብር አንድን ተግባር ለማጠናቀቅ ወይም ግብ ላይ ለመድረስ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች፣ አካላት ወይም ድርጅቶች ጥምረት ነው። ትብብር ከመተባበር ጋር ተመሳሳይ ነው።፡



ምስል 21፡-እርስ በርስ የሚተባበሩ ተማሪዎች

5.2.2.2. መቻቻል

መቻቻል የሚለው ቃል የመነጨው "ጽናት" ከሚለዉ ቃል ሲሆን ትርጉሙ አንድ አካል አስቸጋሪ የአካባቢ ሁኔታን ለመቋቋም ወይም ለመቆጣጠር ያለውን ችሎታ ያመለክታል። መቻቻልን የገነቡ ሰዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥማቸዉ እንኳ የመቋቋም ብቃት አላቸዉ። ብዙውን ጊዜ ቃሉን የምንጠቀመው ሌሎችን የመቀበል ፍላጎታችንን ለማመልከት ነዉ። መቻቻልን ስትለማመዱ የሌላውን ሀሳብ እና እምነት ትቀበላላችሁ። የአንድን ሰው አስተያየት የምታከብሩ ከሆነ ካልተስማማችሁ ወይም ትርጉም የለሽ ሆኖ ብታገኙ እንኳን መቻልን ታሳያላችሁ።

መቻል ህመምን ወይም ችግርን የመቋቋም ችሎታ፣ ጽናት፣ ጥንካሬና ከራስ ለሚለያዩ ወይም ለሚጋጩ እምነቶች ወይም ልምዶች የማክበር የመቀበል ችሎታ ነዉ፤መቻቻል አንድን ነገር የመፍቀድ/ የመቀበል ችሎታ ነዉ።



ምስል 22፡-መቻቻልን እየተለማመዱ ያሉ ተማሪዎች

5.2.2.3. /አካታችነት/

አካታችነት ሁሉንም የሰው ልጆች ማለትም ሴቶችን፣አካል ጉዳተኞችንና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰዎችንና የመሳሰሉትን እኩል ለልማት አስተዋፅየ እንደያበረክቱ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በፍትሀዊነት የማሳተፍ ሂደት ነዉ፡፡

አካታች ልምምዶችን በመለየት ማህበራዊ እና አካላዊ እንቅፋቶችን በመለየት አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች እንዲሳተፉ እና በሁሉም እድገቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ

ማድረግ ይቻላል። አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎችን በትክክል ማካተት በልማት ሂደቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ እና የጥገኝነት ባህርያትን እንዲያስወገዱ ያስችላቸዋል፡፡ ለቤተሰብ እና ለማህበረሰቡ ሰፊ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ የድህነትን ተፅእኖ ይቀንሳል፤ ለአገር ኢኮኖሚያዊ እድገትና ልማት አዎንታዊ አስተዋፅኦ በማድረግ ሁሉን አቀፍ ማህበረሰብ መፍጠር ያስችላል፡፡

5.2.2.4. ትርጉም ያለው ተሳትፎ

ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ ማለት በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴዎች እና ግንኙነቶች ውስጥ ምክንያታዊና ጠቀሜታ ያለዉ ተሳትፎ ማድረግ ማለት ነዉ፡፡



ምስል 23፡-በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ ያሉ ተማሪዎች

5.2.2.5. አክብሮት

አክብሮት ለሰዎች የምንሰጠው አዎንታዊ ስሜት ነው፤በየትኛውም ጊዜና ቦታ እንዲሁም የእድሜ ደረጃ ልዩነት ሳታደርጉ ለሁሉም ሰው አክብሮትን አሳዩ፤አክብሮት እንደ ሸቀጥ የምንገበያየው ነገር አይደለም፤ለሌሎች አክብሮት የሌለው ሰው እራሱን አያከብርም ማለት ነው ምክንያቱም ሰዎችን ስናከብር እኛም በሰዎች ዘንድ ክብርን

እናገኛለን፡፡የእድሜ ባለፀጋ አዛዉንቶችን ማክበር በጣም አስፈላጊና የመልካም እሴቶቻችን መገለጫ ናቸው ፡፡



ምስል 24፡-ለሽማግሌዎች አክብሮት የሚያሳዩ ተማሪዎች

5.2.2.6. እንግዳ ተቀባይነት

እንግዳ ተቀባይነት ማለት ከሌላ ቦታ ወደ ቤታችን፣መንደራችን ወይም ሀገራችን የሚመጣ ሰዉን በአግባቡ ተቀብለዉ ማስተናገድ ማለት ነዉ፡፡ በተጨማሪም

እንግዳ ተቀባይነት በእንግዳ እና በአስተናጋጅ መካከል ያለው ግንኙነት ሲሆን አስተናጋጁ እንግዳ ተቀባይነቱን እና ታማኝነትን ጨምሮ በበጎ ፈቃደኝነት ማሰተናገድ ማለት ነዉ፡፡



ምስል 25፡-ለልጆች በወላጆቻቸው አቀባበል ሲደረግላቸዉ

5.2.2.7. ታማኝነት

ታማኝነት ለገባነዉ መሐላ በቁርጠኝነት የመፈጸም ሁኔታን ያመለክታል። ለወላጆቻችን፤ ለጓደኞቻችን እንዲሁም ለጎረቤቶቻችን ታማኝ መሆን አለብን፤ታማኞች ስንሆን በሰዎች ዘንድ እምነት የሚጣልብንና ተወዳጆች እንሆናለን።

5.2.2.8. የሌሎች ሰዎችን ሃሰብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን

የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን ማለት ሌሎች ሰዎች የሚያቀርቡት አዳዲስ ሀሳቦችን ለመቀበል ወይም ለማክበር ዝግጁ መሆን ማለት ነው።

አንድ ሰው የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ ከሆነ፣ የሌሎችን ሃሳቦች ለማዳመጥ እና ለማገናዘብ ፈቃደኛ ይሆናል ማለት ነው።



ምስል 26፡-የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ የሆኑ ልጆች

5.2.2.9. ተስፋ

ተስፋ አንድን ነገር የመጠበቅ እና የመፈለግ ስሜት ነዉ።ተሰፋ አንዳንድ መረጃዎችን እና ንብረቶችን ለማግኘት በአንድ ሰው ሕይወት ወይም በዓለም ውስጥ ካለ ክስተቶች እና ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ አዎንታዊ ውጤቶችን በመጠበቅ ላይ የተመሠረተ ብሩህ አስተሳሰብ ነው።



ምስል 27፡- ለወደፊት የሚሠራ ልጅ

5.3 የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊነት

ቁልፍ ሐረግ

የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊነት

ተማሪዎች፣ ማህበረሰባዊ እሴቶች ምን እንደሆኑ ከላይ ባለው ይዘት ተምራችሃል።

የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊ ናቸው ፡፡ ምክንያቱም ባህሪያችንን በትክክል እንድንመራ ይረዱናል በተጨማሪም ልዩነቶቻችንን እና ብዝሀነታችን ለማድነቅ እርስበርስ ለመተባበር፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ፣ ሐቀኛ እና

ለሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ሁሉ አክብሮት ለማሳየት ይጠቅሙናል፡፡

ተግባር 6፡-

በቡድን ሆናችሁ ስለማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊነት ተወያዩና መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ ።



ምስል 28፡- አራት ዋና ዋና የማህበረሰብ እሴቶች

ተግባር 7፡

ከላይ ባለው ምልክት ላይ የተጻፉትን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. **ምስሉ ላይ የተጻፉት አራቱ ነገሮች ምንን ያመለክታሉ?**
2. **ምልክቱ ስለ ማህበረሰቡ እሴቶች አስፈላጊነት ምን ያሳያል?**

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

- **ማህበረሰብ የምንለው በአንድ አካባቢ አብረው የሚኖሩ ሰዎች ስብስብን ነዉ።፡**
- **ማህበረሰብ እንደ ገጠር፣ አርብቶ አደር፣ ከተማ እና የተለያዩ ሀይማኖታዊ የማህበረሰብ አካላትን አካቶ የያዘ ነዉ።**
- **የማህበረሰብ እሴቶች የማህበረሰቡ አባላት የሚጋሩት እምነቶች ናቸው።**
- **መተባበር፣ መቻቻል፣ ትርጉም ያለው ንግግር፣ አክብሮት፣ ታማኝነት፣የሰዉን ሀሳብ መቀበል እና ተስፋ ዋና ዋና የማህበረሰቡ እሴቶች ምሳሌዎች ናቸው።**

☞የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ባህሪያችንን በአግባቡ እንድንመራ፣ ብዝሃነትን እንድናደንቅ፣ እርስ በርሳችን እንድንተባበር እና ሌሎች የማህበረሰቡን አባላት እንድናከብር የሚያስችሉን እሴቶች ናቸዉ።

የምዕራፍ አምስት የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ትዕዛዝ አንድ፡- አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ “እውነት” ስህተት ከሆነ ደግሞ “ህሰት” በማለት መልስ ስጡ።

1. በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የገጠር ማህበረሰቦች ናቸው፡፡

2. መተባበር ማለት ተባብሮ መሥራት እና መደጋገፍ ማለት ነው።

3. ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ተገቢውን ክብር መስጠት ከማክበር ጋር የተያያዘ ነው።

4. የገበሬዎች መንደር በገጠር ማህበረሰብ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

5. ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ የማህበረሰብ እሴቶች አጋዥ ናቸው።

ትዕዛዝ ሁለት፡- ከዚህ በታች ከተሰጡት ቃላት ወይም ሐረጋት ትክለኛዉን በመምረጥ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡

የተሰጡት ቃላት /ሀረጋት

የማህበረሰብ እሴቶች፣ የማህበረሰብ እሴቶች አስፈላጊነት፣

ማህበረሰብ ፣ የከተማ ማህበረሰብ ፣ ታማኝነት ፣አክብሮት

1. በአንድ የተወሰነ ክልል ውስጥ አብረው የሚኖሩ የሰዎች ስብስብ

----------ይባላሉ፡፡

2. ሰፊ የሆኑ አብረዉ የሚኖሩ ሰዎች ስብሰብ የከተማ _____ ናቸው።

3. ትክክል የሆነውን ነገር ማድረግ ---------- ይባላል፡፡

4. በሁሉም ግለሰቦች ዘንድ የተለመዱ የጋራ እምነቶች _____ ተበለዉ ይጠራሉ፡፡

5. ለሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ክብር መስጠት _____ ይባላል፡፡

ምዕራፍ ስድስት

የአካባቢ ባህሎችን ማወቅ

ከምእራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

- የባህል ጽንሰ-ሐሳብን ታብራራላችሁ
- የአካባቢ ባህል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትረዳላችሁ
- የአካባቢ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎችን ትዘረዝራላችሁ
- ባህላዊ እሴቶቻቸውን ታደንቃላችሁ
- የተለያዩ ማህበረሰቦችን ባህላዊ እሴቶች ታሳያላችሁ

6.1 የባህል ምንነት

ቁልፍ ሐረግ

ባህል

ባህል የአንድ ህዝብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ባህል ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፈው በአፈ-ታሪክና በጽሑፍ ነው፡፡ ሰዎች ባህላቸውን በሙዚቃዎቻቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በልብሳቸው፣ በምግባቸው እና በሌሎች ተግባራት ያሳያሉ፡፡ የህዝቦች ባህል በወግና ልማዳቸው (ትውፊቶቻቸው) ላይ የተመሰረተ ነው።

ተግባር 1፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩ እና መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

1.ባህል ምንድን ነው?

2.ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት ይተላለፋል



ምስል 29፡-አዛዉንቶች ለልጆች ታሪክ ሲነግሯቸው

ተግባር 2፡

ምስሉን በቡድን በመሆን ከተመለከታችሁ በኋላ የተገነዘባችሁትን ለመመህራችሁ ንገሯቸው፡

6.2 የአካባቢያዊ ባህል ምንነት

የአካባቢያዊ ባህል በምንኖርበት አካባቢ በዕለት ተዕለት ኑሯችን እርስ በርስ የምንጋራቸውን የማንነታችን መገለጫዎች ናቸዉ፡፡



ምስል 30፡- የሀመር ማህበረሰብ ባህል

ተግባር 3፡

ከላይ ያሉትን ጽሑፍና ምስሎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. **አካባቢያዊ ባህል ምንድን ነው?**

2. ሥዕሎቹ ስለ አካባቢያዊ ባህል ምን ይነግሯችኋል?

3. በሥዕሉ ላይ ያሉት ሰዎች ምን ይጋራሉ?

4. በአካባቢያችሁ ካሉ ሰዎች ጋር ከምትጋሯቸው ወግና ልማዶች (ትውፊቶች) ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ?

6.3 የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች

ቁልፍ ሐረግ

የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች



ምስል 30፡-ተማሪዎች ከክፍል ውጪ እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ



ምስል31፡- ሰዎች የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁሶች የሚገኙበትን ቤተ-መዘክር ሲጎበኙ



ምስል 32፡- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወቱ ሙዚቀኞች ባንድ

የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች የምንላቸው ቋንቋ ፣ ምልክቶች ፣ ደንቦች፣ እሴቶች፣ አልባሳት፣ ሙዚቃ፣ ጥበብ፣ እምነት፣ ምግብ እና ሃይማኖት ናቸው።

ተግባር 4፡ ከላይ በቀረቡት ጽሑፉና ስዕሎች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች ምንድናቸው?
2. በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ዋና ዋና የባህል መገለጫዎችን በቡድን ለዩና መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው።.

6.4 የአካባቢያዊ ባህል አስፈላጊነት

ቁልፍ ሐረግ

የአካባቢያዊ ባህል አስፈላጊነት

አካባቢያዊ ባህል ብዙ ጥቅሞች አሉት። ለምሳሌ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች አሉት። በተጨማሪም ሕይወታችንን ለማሻሻል፣ ከሌሎች የማህበረሰባችን አባላት ጋር ግንኙነት ለመመስረት፣ ታጋሽ እንድንሆን (እንድንቻቻል) እና ለህብረተሰባችን አጠቃላይ ደህንነት አስተዋፅዖ እንድናበረክት ይረዳናል።



ምስል 33፡-የአንድ አከባቢ ነዋሪዎች በአብሮነት መርሃ ግብር



ምስል 34፡-እርስ በእርስ እየተረዳዱ ያሉ የአንድ ማህበረሰብ አባላት



ተግባር 5፡

ከላይ በቀረቡት ስዕሎች ላይ ተመስርታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

አካባቢያዊ ባህል ለግለሰቦች እና ለማህበረሰብ ያለውን አስፈላጊነት በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ ፡፡

6.5 የማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች

ቁልፍ ሐረግ

ባህላዊ እሴቶች

ባህላዊ እሴቶች ማህበረሰብ የሚመሠረትባቸው ዋና ዋና መርሆች እና ሀሳቦች ናቸው።

ተግባር 6፡-

ከላይ ባለው ጽሑፍ ላይ ተመስርታችሁ በጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ባህላዊ እሴት ማለት ምን ማለት ነዉ?

የምእራፍ ስድስት ማጠቃለያ

- ባህል የአንድ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው።
- ባህሎች በሙዚቃ፣ በሃይማኖት፣ በአለባበስ፣ በአመጋገብ እና በተግባራት ሊገለጹ (ሊታዩ) ይችላሉ፡፡
- አካባቢያዊ ባህል ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ በዕለት ተዕለት ተግባሮቻቸው የሚጋሩት ማንኛውም ነገር ነው። አካባቢያዊ ባህል የጋራ ልምድ እና ልማዶችን ያካትታል.
- ቋንቋ፣ እሴቶችና ቁሳዊ ነገሮች የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች ናቸው።
- ባህላዊ እሴቶች የማህበረሰብ መሠረት የሚሆኑ ዋና ዋና መርሆዎች እና ሀሳቦች ናቸው፡፡

📂የተለያዩ ሥርዓቶች ወይም የበዓል አከባበሮች የወግና ልማድ) አካል ናቸው።

የምእራፍ ስድስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ትዕዛዝ አንድ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ “እውነት” ስህተት ከሆነ ደግሞ “ህሰት” በማለት መልስ ስጡ።

1. ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ በጽሑፍ ብቻ ይተላለፋል።
2. ትውፊቶች እና እምነቶች የባህል መሰረቶች ናቸው።
3. በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በአካባቢያዊ ባህል የጋራ ልምድ አላቸው።።
4. የአንድ ማህበረሰብ አባላት እርስ በእርሳቸው መቻቻል የለባቸውም።።

ትዕዛዝ ሁለት፡- ለሚከተለዉ ጥያቄ መልስ ስጡ

1.የአካባቢያዊ ባህል ዋና ዋና መገለጫዎችን ዘርዝሩ

_____

_____

_____

_____